


ማብራሪያ

ኢስላም የሰውን ልጅ ትክክለኛው ፍኖት ላይ ስለሚያኖረው ሕሊናውንም ካለማወቅ እና ከከንቱ እምነት ነፃ ያወጣዋል። ከየት መጣን፣ ለምንስ መጣን እና ወደየት ነው የምንጓዘው የሚሉ የሰው ልጅን አዕምሮ ለዘመናት ሲያንኳኩ ለኖሩ ውስብስብ ጥያቄዎች መልስ ይሰጣል።

አዕምሮን ነፃ ማውጣት ማለት ግን ከሁሉም ግድቦች ያመለጠና እውነትን እውነት እብለትን እብለት ማለት እስኪያቅተው ድረስ ልጓም አልባ ይሁን ማለትም አይደለም። ኢስላም አዕምሮን ነፃ የሚያወጣው ከአላህ ውጪ ከሚመለክ አካልና ከዱንያ ውዥንብሮች ነው። ኢስላም ወደ ፍጥረተ-ዓለሙ በጥልቀት ወደ መመልከት አነሳስቷል። ቁርአን ወደ ሰማያትና ምድር በጥልቀት የሚያዩና የሚያስተነትኑትን አወድሷል። ይህ ማስተንተን ታዲያ በአላህ ላይ ያለን ኢማን ይጨምራል።

ኢስላም ለዕውቀትና አዋቂዎች ልዩ ቦታን ይሰጣል። ምድር ላይ የአላህን የምትክነት ኃላፊነት ለመወጣት እና ለማሳመር፣ ለሙስሊሙ ዓለምና ለሰው ልጅ አጋዥ ኃይል የሆነ ማንኛውንም ዕውቀት አልቋል። ኢስላም በተለያየ ዘርፍ ያሉ አዋቂዎችን አወድሷቸዋል። ደረጃቸውን ከፍ አድርጓል። ይህን አስመልክቶ ብዙ የቁርአን እና ሐዲስ አናቅፅ አሉ።

قُلْ هَلْ يَسْتَوِي الَّذِينَ يَعْلَمُونَ وَالَّذِينَ لَا يَعْلَمُونَ

«እነዚያ የሚያውቁና እነዚያ የማያውቁ ይስተካከላሉን?» በላቸው።››(አዝ-ዙመር 9)

መልዕክተኛው (ሰዐወ) ማንኛውንም መልካም ነገር ከማንም በደስታ ይቀበሉ ነበር። ዓረቦች ዘንድ በጦርነት ወቅት የማይታወቀውን የፔሪሺያውያን የጦር ልምድና እስትራቴጂ የነበረው የምሽግ ቁፋሮ ሐሳብ ሲቀርብላቸው በደስታ ተቀብለዋል። ኢማም ሐሰን አል በናም ለዚህ ነበር የኢስላምን አብራኮች መሰረታዊ ማንነታቸውን በጠበቀ መልኩ ወደ መሻሻል በዚህች መርህ የተጣሩት። በህክምና፣ የጠፈር ምርምር፣ መሪነት፣ ስነ-ህንፃ፣ ማምረት እና ግብርና ወዘተ ሀሁሉም ዘርፍ ላይ ባለ መልካም ነገር ሁሉ የሙስሊሙ ማህበረሰብ የተገባ ነው።

ዓብዱራህማን ሰዒድ

1441